June 18, 2019 QuickNotes

**በሰመር ወቅት ተማሪዎች ነፃ ምግብ ይሰጣቸዋል።**
በበርካታ የሰመር ት/ቤቶች ወይም የመዝናኛ ፕሮግራሞች የሚገኙ ተማሪዎች የሞንትጎመሪ ካውንቲ (Montgomery County) የሰመር ፕሮግራም ምግቦችን ይቀበላሉ። ፕሮግራሙ በአነስተኛ-ገቢ የሚገኙ ተማሪዎች የት/ቤት ቁርስና ምሳ በማያገኙበት በሰመር ወራት አልሚ ምግቦችን ማግኘት መቻላቸውን ያረጋግጣል።

በካውንቲው ውስጥ በሣምንቱ የሥራ ቀናት ነፃ ምግብ የሚሰጥባቸው ቦታዎች በግምት 120 ጣቢያዎች ሲሆኑ **ከጁን 17 ጀምሮ** (በየጣቢያው የሚጀመርባቸው ቀኖች ይለያያል)። 18 ዓመት ወይም አነስተኛ ዕድሜ ያላቸው ልጆች፣ የአካል እና የአእምሮ ጉዳተኞች እስከ 21 ዓመት ዕድሜ እስኪሞላቸው ድረስ ምግብ ለማግኘት/ለመቀበል ብቁ ናቸዉ።

በማናቸውም የተለየ የካውንቲው ሠመር ፕሮግራም ላልተመዘገቡ በካውንቲው በሞላ በርካታ ጣቢያዎች ላይ ጎራ በማለት ምሣ ይሰጣቸዋል። ስለ ቦታዎችና የምግብ ሰኣቶች የተለየ መረጃ ለማግኘት፡- እዚህ ጠቅ ኣድርጉ።

ለተጨማሪ መረጃ፣ የምግብና የኣመጋገብ ኣገልግሎቶች ክፍል/Division of Food and Nutrition Services በ301-284-4900 ይደውሉ።

**የትምህርት ቦርድ ለ 2020 የበጀት ዓመት $2.68 ቢልዮን ዶላር የስራ ማስኬጃ በጀት አፅድቋል**
የሞንትጎመሪ ካውንቲ የትምህርት ቦርድ ጁን 11፣ የ 2020 የባጀት ዓመት የሥራ ማስኬጃ ባጀትን በሙሉ ድምፅ ወስኗል። የ $2.68 ቢሊዮን ባጀት ከአሁኑ የባጀት ዓመት በ $80.14 ሚሊዮን ከፍ ያለ ተጨማሪ ወጪን ያካትታል።

ከ $80.14 ሚሊዮን የሥራ ማስኬጃ ጭማሪ አብዛኛው እያደገ ለመጣው የተማሪዎች ቁጥር የሚሰጠዉን አገልግሎት ለማስቀጠል/ለመጠበቅ፤ እየጨመረ የመጣውን የሥራ ማስኬጃ ወጪ ለመምራት/ለማከናወን፤ ቀጣይነት ያላቸዉን ደሞዞችን እና ጥቅማጥቅሞችን ፈንድ ለማድረግ፤ እና ለሁሉም ተማሪዎች የእድሎችን ተደራሽነት ክፍተት ለመዝጋት ቁልፍ በሆኑ የስራ መስኮች እና የትምህርት ጥራት ላይ ኢንቨስት ለማድረግ ይውላል።

እንዲሁም ባጀቱ ፕሮግራሞችን ለማሻሻል፣ ለጠንካራ የአካደሚክ እና የሙያ ስራ እድሎች ተደራሽነት እድሎችን ለማስፋት፣ ትምህርት ለማራዘም፣ የቋንቋ እድሎችን ለመስጠት፣ አካላዊ፣ ማህበራዊ እና ስነልቦናዊ ደህንነት ላይ ለማተኮር፣ ውጤታማ የስራ ግብረኃይል ስብጥር ለመቅጠር እና በስራ ለማቆየት፣ እና ለአፈጻጸም ብቃትና ዲስትሪክቱ የሚያደርጋቸውን ጥረቶች ለማጠናከር በሚረዱ ቁልፍ መስኮች ላይ የገንዘብ ምደባን ያካትታል። ይበልጥ ለማወቅ ይህንን ድረ-ገጽ https://www.montgomeryschoolsmd.org/departments/budget/ ይጎብኙ።

**ቅድመ ሙዓለህጻናት/ሄድ ስታርት ለቤተሰቦች ነፃ የሠመር ዝግጅት ይኖረዋል**

ቅዳሜ፣ ጁላይ 13 ከ 11 a.m. እስከ 3 p.m በዊተን ሪጅናል ፓርክ/Wheaton Regional Park.*በሚካሄድ የሄድስታርት ፓርቲ (Head Start Party in the Park)* ላይ የሞንትጎመሪ ካውንቲ ቤተሰቦች *እንዲሳተፉ* ተጋብዘዋል። በባቡር ጣቢያ ፓርክ ላይ የሚካሄደው ዝግጅት በተባባሪነት የሚደገፈው/ስፖንሰር የሚያደርጉት የጤና እና ሰብአዊ አገልግሎት መምሪያ (DHHS) የማህበረሰብ እንቅስቃሴ ኤጀንሲ፣ የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS)፣ የሞንትጎመሪ ፓርኮች፣ የትናንሽ ልጆች አገልግሎት/DHHS Early Childhood Services፣ እና የሞንትጎመሪ ካውንቲ የህዝብ ቤተመጻህፍት/ላይብራሪዎች ናቸው። የዊተን ሪጅናል ፓርክ የሚገኘው በ 2000 Shorefield Road ላይ ነው።

ስለ Pre-K/Head Start ፕሮግራም መረጃ መስጠት እና በስፍራው ምዝገባ ማድረግን የሚያካትት ስለሆነ የ4 ዓመት ልጆች ያሏቸው ወላጆች ይህንን ዝግጅት እንዲሣተፉ እናደፋፍራለን። በርካታ የማህበረሰብ ኤጀንሲዎች እና ድርጅቶች በዝግጅቱ ላይ በመሣተፍ ጠቃሚ የትምህርት መርጃዎችን ለተሳታፊዎች ያበረክታሉ። ይህ በነፃ የሚካሄድ ዝግጅት DJ፣ የምግብ ገበታዎችን/መሸጫ፣ ፊት ማቅለም፣ በፊኛ የተመሰሉ እንስሣት፣ እና ለልጆች ሌሎችንም እንቅስቃሴዎች ይጨምራል። ስለዚህ ዝግጅት ይበልጥ በእንግሊዝኛ እና በስፓንሽ ለማወቅ እባክዎ እዚህ ጠቅ ያድርጉ።

ስለ 2019-2020 የትምህርት ዓመት Head Start/Pre-K ምዝገባ ይበልጥ ለማወቅ እባክዎ እዚህ ጠቅ ያድርጉ ወይም በስልክ ቁጥር፦ 240-740-4530 ይደውሉ።

**እንደገና ተመልሰናል! የ2019 የትምህርት-መጀመርያ በአል እያምልጥዎት**

የ 2018–2019 የትምህርት ዓመት ወደ ማብቂያዉ ደርሷል፣ እናም MCPS ከአሁኑ ስለሚቀጥለው ዓመት አሻቅቦ ማዬት ጀምሯል። ለ 2019–2020 የትምህርት ዓመት በሚጀመረው የደስታ ጊዜ ከእኛ ጋር ይሳተፉ! የ MCPS ተማሪዎች በጠቅላላ እና ቤተሰቦቻቸው ቅዳሜ፣ ኦገስት 24 ከ 10 a.m.እስከ 2 p.m. በ Westfield Wheaton በሚካሄደው የ "MCPS Back-to-School" አውደ ርዕይ እንዲሣተፉ ተጋብዘዋል። "Back-to-School" አውደ ርዕይ የትምህርት ዓመት ሲጀመር ከመንግስት ኤጀንሲዎች እና ከማህበረሰብ አጋሮች ስለ ትምህርት ሲስተም ፕሮግራሞች እና አገልግሎቶች ለማወቅ በእጅጉ ጠቃሚ መንገድ ነው። የትምህርት ቤት ሥራ ባልደረቦች በስፍራው ተገኝተው ስለ ሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ስርአተትምህርት/ከሪኩለም እና ፕሮግራሞች ጥያቄዎችን ይመልሳሉ።

ለጠቅላላ ቤተሰብ የህፃናት እንቅስቃሴዎችን ጨምሮ የልጆች እና የአዋቂዎች የጤና ምርመራ፣ ነፃ መዝናኛ እና በነፃ የሚሰጡ ነገሮች ይኖራሉ! አውቶቡሶች ይቀርባሉ፣ ቦታዎቹ ተለይተው ይገለፃሉ።

የሠመር ወቅት Back-to-School አውደ ርዕይ ድረ-ገጽ ካላንደርዎ ላይ ምልክት አድርገው ይከታተሉ፣ እንዲሁም ወቅታዊ መረጃዎችን ለማግኘት በ Facebook እና Twitter ላይም ይከታተሉን። #1stDayReady

ስለ አውደ ርእዩ የበለጠ መረጃ ለማግኘት፣ Back-to-School Fair ድረ-ገጽ ይጎብኙ ወይም Department of Communications በስልክ ቁጥር፦ 240-740-2837 ይደውሉ።

**ለ 2019-2020 የትምህርት አመት ተፈላጊ ክትባቶች**

በ 2019–2020 ወደ ሰባተኛ ክፍል የሚገቡ ልጆች በሙሉ የ ቴታነስ - Tetanus-diphtheria-acellular pertussis (Tdap) እና መንንጃይትስ - Meningococcal meningitis (MCV4) ክትባቶችን የትምህርት ዓመት ከመጀመሩ በፊት መውሰድ አለባቸው። በተጨማሪ፣ ከ 8ኛ እስከ 12ኛ ክፍል ወደ ሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) አዲስ የሚገቡ ተማሪዎች በሙሉ አንድ Tdap እና MCV4 ክትባት መዉሰድ ይጠበቅባቸዋል። ተማሪዎች የ Tdap እና MCV4 ክትባት ማስረጃ እንዲያቀርቡ ይጠበቃል።

ወላጆች ዶክተራቸውን እንዲያነጋግሩ እና ልጃቸው በትክክል ክትባት መውሰዱ(ዷ)ን ማረጋገጥ እና በተቻለ ፍጥነት ማስረጃቸውን ለትምህርት ቤት ነርስ ማቅረብ አለባቸው፣ ነገር ግን የ 2019–2020 የትምህርት ዓመት የመጀመሪያው ቀን **ማክሰኞ፣ ሴፕቴምበር 3 ሳይዘገይ መሆን አለበት።**

**ሠመር ለማንበብ በጣም ጥሩ ጊዜ ነው!**
በሞንትጎመሪ ካውንቲ የህዝብ ቤተመጻህፍት/ፐብሊክ ላይብራሪዎች (MCPL) ከጁን 15 ጀምሮ እስከ ኦገስት 31 በሚካሄደው የዚህ ዓመት የሠመር ምንባብ ፕሮግራም ጠቀላላ ተማሪዎች እንዲሣተፉ ተጋብዘዋል። የዚህ ዓመት ዓብይ ርእስ "A Universe of Stories" በሁሉም እድሜ ክልል ያሉ ልጆች ህልማቸው ትልቅ እንዲሆን፣ በራስ መተማመን እንዲኖራቸው፣ እና የራሳቸውን ታሪክ እንዲፈጥሩ ያበረታታል። ዝግጅቱ በዋናነት ጨረቃ ላይ የታረፈበትን 50ኛ ዓመት ክብረ በዓል መሠረት ያደረገ ነው።

አዲስ የተወለዱ አራስ ህፃናት እስከ 12 ዓመት እድሜ ለጋ ወጣት ልጆች፣ከ 13 - 17 ዓመት ዕድሜ ክልል የሚገኙ ልጆች በድረ-ገጽ ወይም ከጁን 15 እስከ ኦገስት 31 በማናቸውም ቅርንጫፍ እንዲመዘገቡ ተጋብዘዋል።

ጨዋታ፣ ቀልድ፣ ፊዝ፣ አዝናኝ ትምህርታዊ እንቅስቃሴዎችን የሚያነቡ እና/ወይም በአዝናኝ ትምህርታዊ እንቅስቃሴዎች የሚሳተፉ ተሳታፊዎች ሽልማት፣ (አቅርቦቱ እስካለ ድረስ)፣ ለላይብራሪ ወዳጆች ቫውቸሮች፣ ከሞንትጎመሪ ካውንቲ የመጻህፍት መደብር፣ ወይም የሎተሪ ግብአቶች ሊያገኙ ይችላሉ/vouchers to a Friends of the Library, Montgomery County (FOLMC) bookstore; or raffle entries።

የሠመር ማንበብ እና መማር በሞንትጎመሪ ካውንቲ ላይብራሪ ወዳጆች እና የአካባቢ ቤተመጻፍህት ቻፕተር ወዳጆች ልግስና ድጋፍ የሚካሄዱ በርካታ የተለያዩ ፕሮግራሞችን እና ሁነቶችን ያካትታል። የፕሮግራሞቹ/የመርኃግብሮቹ የጊዜ ሰሌዳ በቤተመጻሕፍት ሁነቶች ካለንደር/Library's calendar of events ላይ ይገኛል።

ስለ ፕሮግራሙ የበለጠ መረጃ ለማግኘት ይህንን ድረ-ገጽ MCPL website ይጎብኙ።

በተጨማሪ፣ የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ተማሪዎች በዚህ ሠመር ሁለት ታላላቅ ግብአቶችን/resources ለማንበብ ተደራሽነት አላቸዉ:- "Capstone Interactive Library eBooks እና OverDrive Summer Read using Sora"።

እነዚህ ሁለት ፕሮግራሞች የትም ቦታ፣ ምንጊዜም ልብወለድ እና ልብወለድ ያልሆኑ ርእሶችን በማንበብ እርካታ ለማግኘት ማናቸውንም በነፃ ለመጠቀም የሚያስችል መሣሪያ/device በመጠቀም በሠመር ወቅት አንባቢነትን ለመቀጠል ያስችላሉ።

"Capstone Interactive Library" ቤተመጻህፍት/ላይብራሪ ለኤለመንተሪ እና ለመካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች በት/ቤት፣ በቤት፣ ወይም በጉዞ ላይ የሚነበቡ በሺዎች የሚቆጠሩ eBooks በነፃ ይሰጣል። እነዚህን "eBooks " በላፕቶፕ፣ ዴስክቶፕ፣ ወይም በታብሌት (laptop, desktop or tablet.) መጠቀም ይቻላል። ከሁሉም በላይ፣ "Capstone Interactive eBooks) የጽሑፍ ፍሬ ሃሳቦችን ማድመቂያ፣እና በፕሮፌሽናል የድምፅ አርቲስቶች ሪኮርድ የተደረገ አንባቢ-ድምፅ የሚሣሰሉ ወሳኝ የሆኑ ድጋፎችን ይሰጣል። ቀለል ያለዉ ዳሰሳ ተማሪዎች ምርጫቸዉ የሆነዉን  Capstone እንደ:- "spunky Katie Woo" ወይም "spirited Yasmin" ከ "PebblePlus" መጽሐፍት ውብ የሆኑ ፎቶግራፎች፣ እና አስደሳች ምንባቦችን እንደ *Library of Doom* በ Michael Dahl የተደረሱ የመሳሰሉትን እንዲያገኙ ይጋብዛቸዋል/ያጓጓቸዋል።

ይህንን መግቢያ/login መረጃ በመጠቀም ርእሶችን በሙሉ ይመልከቱ:-

www.mycapstonelibrary.com
Login: capstonesummer
Password: interactive19

በዩ.ኤስ እና በካናዳ OverDrive Summer Read የተሰኘው የትምህርት ቤቶች የሠመር ምንባብ ፕሮግራም ተማሪዎች አመቱን በሙሉ ከማንበብ እንዳያቋርጡ ለማበረታታት የተነደፈ ነው። የዚህ ዓመቱ የ 10-ሣምንት ፕሮግራም ከጁን 6 እስከ ኦገስት 15 ድረስ ይካሄዳል። OverDrive ከምንግዜም በላይ በርካታ ርእሶችን ይሰጣል። ለሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ተማሪዎች ሠላሳ ነጻ እና ለወጣት እና ልጅግር ጎልማሳ በአንድ ላይ የሚጠቅሙ eBooks (እና የተመረጡ audiobook እና Read-Along) አማራጮች ይገኛሉ። እነዚህ ርእሶች በ "Sora app" ላይ በግልጽ ታዋቂ ስለሆኑ፣ ተማሪዎች ቀጣዩን መጽሐፋቸውን ለማግኘት እና እየተዝናኑ ለማንበብ ይቀላቸዋል። ተማሪዎች ሁሉንም ካነበቡ፣ Sora ከመተዋቸው በፊት ዘወትር ከትምህርት ቤታቸው ቤተመጻህፍት የበለጠ/ብዙ መጻሕፍትን መፈለግ/ማግኘት ይችላሉ። እንዲሁም ለሠራተኞች 100 ፕሮፌሽናል ርእሶች ይገኛሉ።

ከ "OverDrive" የሠመር ምንባብ ርእሶችን በዚህ የ Sora ድረ-ገጽ ላይ ገብተው ይፈልጉ፡-
https://soraapp.com
Login: MCPS username
ይለፍቃል፡- MCPS password

**የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ተመራቂዎችን ድምጽ ያዳምጡ (Hear the Voices of MCPS Grads)**

ከሜይ 24 ጀምሮ እስከ ጁን 13 በተካሄዱት የምረቃ ስርአቶች ከ 11,000 በላይ የ MCPS ተማሪዎች ዲፕሎማዎችን አግኝተዋል።

የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የ2019 ክፍል አባላትን ታሪኮቻቸውን እና ፎተግራፎችን የሚያመለክት ቪድዮ በድረ-ገጽ አዘጋጅቷል። ጥቂት ተመራቂዎች በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ስለነበራቸው ቆይታ እና የወደፊት እቅዶቻቸውን በሚመለከት ያካፈሉትን ሃሳብ ለማዳመጥ/ለመስማት ድረ-ገጹን ይጎብኙ። ለ 2019 ተመራቂዎች፣ እንኳን ደስ አላችሁ!

የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ተመራቂዎች ድምፅ

**የ Give BACKpacks ዘመቻን ይደግፉ**

ለሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ተማሪዎች የገንዘብ ድጋፍ/raise funds፣ ቦርሣዎችን፣ እና የት/ቤት መማሪያ ቁሳቁሶችን ለማሰባሰብ እና ስርጭቱን ለማስተባበር 7ኛውን ዓመታዊ የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ MCPS "MCPS GIVE BACKpacks" ዘመቻ ይቀላቀሉ።

ለአንድ ተማሪ የትምህርት ቤት መማሪያ ቁሳቁሶች የታጨቀበት ቦርሣ በትንሹ በ $10 መስጠት ይችላሉ። በትምህርት ዓመት መጀመሪያ ላይ በተቻለ መጠን የት/ቤት ቦርሣ (backpack) እና የትምህርት ቁሣቁሶችን ለበርካታ ተማሪዎች የመስጠት ግብ በመያዝ የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) በሠመር ወቅት ያዛል። ጁን፣ ጁላይ እና ኦገስት ለማዘዝ በጣም ወሣኝነት ያላቸው ወሮች ናቸው።

በመቶዎች የሚቆጠሩ የማህበረሰባችን ለጋሽ ሰዎች ምስጋና ይግባቸውና በ 2018-2019 ዘመቻ ወቅት፣ ዲስትሪክቱ ቁጥራቸው ከ18,500 የሚበልጡ የትምህርት ቤት ቦርሣዎች/backpacks ለሚያስፈልጋቸው ተማሪዎች ተሰጥቷል። በዚህ ዓመት፣ የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) 20,000 የትምህርት ቤት ቦርሣዎችን/backpacks እና የመማሪያ ቁሳቁሶችን በጠቅላላ በእኛ ትምህርት ቤት ሲስተም ለሚገኙ ተማሪዎች ለማዳረስ $200,000 የገንዘብ ድጋፍ የማሰባሰብ ግብ አለው።

ስለዚህ ዘመቻ በማስተዋወቅ/ለሌሎችም በመንገር ከባልደረቦች፣ ቤተሰብ፣ ጓደኞች፣ እና የማህበረሰብ አባላት ጋር የዘመቻ በራሪ ወረቀት በማሠራጨት ይርዱ። እያንዳንዱ ልግስና ድጋፍ የሚያስፈልገውን/የሚያስፈልጋትን ተማሪ ይረዳል።

ስለ "GIVE BACKpacks" የበለጠ ለማወቅ፣ እባክዎ ይህንን ድረ-ገጽ ይጎብኙ www.mcpsgivebackpacks.org።